## የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ

**ETHIOPIAN DEMOCRATIC HIBREHIZB UNITY MOVEMENT (EDHUM)**

*P.O. Box 73796 * Washington D.C. 20056-3796; E-mail: edhum2000@yahoo.com*


======= ======= =======

# ለለውጥ የቆመው ኃይል (የተቃዋሚው ጎራ) እና ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት

## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) ለውይይት የቀረበ፡

**ምርጫ፤** በነዚኽ ሦስት ፊደላት የሚገለፅ ይኽ ኃይለ-ቃል ከአንድ በላይ ከሆኑ ነገሮች፣ ጉዳዮች ወይም አሳቦች፣ ወዘተ. መኻል አበላልጦ፣ አወዳድሮና አመዛዝኖ ጠቀሜታው የተሻለ (የበለጠ) ሆኖ የተገኘውን ወይም ነው (ይሆናል) ተብሎ የታሰበውንና የታመነበትን ለመያዝ፣ ለመውሰድ፣ ወይም ለመወገን የሚያስችል፣ በአጠቃላይ ሰብዓዊ ተፈጥሮ ያለው ሁሉ በቀን-ተቀን ሕይዎቱና ኑሮው የሚገለገልበት፣ ውስጣዊ ምኞቱንና አጠቃላይ ፍላጎቱን የሚወስንበት፣ ነፃነቱን የሚያረጋግጥበትና መብቱን የሚያስከብርበት ዘዴ/መንገድ ነው።

ይኽንን ቃል ለዚኽ ፅሑፍ ምክንያት በሆነው የፖለቲካ ይዘቱ ላይ ብቻ፣ በተለይም ደግሞ በአገራችን በኢትዮጵያ ከዘጠኝ ወራት በኋላ ስለሚደረገው ሕዝብ ድምፁን እንዲሰጥበት ስለሚጠየቅበት አጠቃላይ ምርጫ በተባለው ኩኔት (ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት) ላይ አተኩረን በአጭሩ እንመለከታለን።

አገራችን የምትገኝበትን አጠቃላይ ውጥረት የተሞላበት የፖለቲካ ሁኔታና የፖለቲካ ድርጅቶች ከሚከተሏቸው የተለያዩ የትግል ስልቶች አኳያ በአሁኑ ጊዜ ስለ ምርጫ የሚሰነዘርን አስተያየት እንዲሁ በግልቡ በመውሰድ ምናልባት በአንዳንድ ወገኖች ያላስፈላጊና አልፎም አዘናጊ ተደርጎ እንደሚወሰድ እንገምታለን።

የግንቦት ዘጠና-ሰባት ወደር-የሌለው እንቅስቃሴ መክሰም፣ የአገዛዙ በነፃ የውድድር ሕግ የመገዛት ፍላጎትም ሆነ ዝግጁነት አለመኖር፣ በአጠቃላይ ምርጫን በመሰለ በሰላማዊ መንገድ በሚደረግ እንቅስቃሴ ሁሉ ተስፋ ማጣት፣ ወዘተ በብዙ ወገኖች ዘንድ ያለ ስሜት ስለሆነ ስለ ምርጫ ብዙ ውይይት ባይደረግና አነስተኛ ትኩረት የሳበ ብቻ ሣይሆን እንዲያውም የተዘጋ መዝገብ (ፋይል) ተደርጎ መታየቱ ላይገርም ይችላል።

በአሁኑ ጊዜ ይኽንን ነጥብ ሁሉም እንዲያስብበትና እንዲወያይበት ስናቀርብ ምርጫን - በተለይ ይኽን ውጤቱ ምን እንደሆነ አስቀድሞ የታወቀና የተወሰነ ምርጫ-ሁለት-ሽህ-ሁለትን - በነጠላውና በግልቡ በመውሰድ ሣይሆን ይኽ ምርጫ በሂደትነቱና በትግል ስልትነቱ ከአጠቃላዩ ለአዲስ ዴሞክራሲያዊ የኅብረተሰብ ግንባታ ለሚደረገው እልህ-አስጨራሽ ትግል ከሚኖረው ጠቀሜታ አኳያ በመነሣት ሲሆን፣ ሁሉም እኩል ክብደትና ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ ያስተናግደዋል የሚል ብዥታ ኖሮን አይደለም። እንዲያውም አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች በጉዳዩ ላይ መወያየት መጀመር የነበረባቸው በጣም ቀደም ብለው ነበር ብሎ ድርጅታችን ያምናል።

በዓለም ላይ ያሉ አገሮች ሁሉ አንድ ዓይነት ወይም ተመሣሣይ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲኖራቸው መቸም አይጠበቅም። እያንዳንዱ አገር የሚኖረው የአስተዳደር ሥርዓት በአገሩ ባለው ተጨባጭ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የታሪክ፣ የእምነትና ሌሎች ሁኔታዎች ምክንያት ሊለያይ ይችላል። ሆኖም ግን በተለይም ድኅረ-ቀዝቃዛው ጦርነት በዓለም-አቀፍ ደረጃ

ተቀባይነት ያላቸው መሠረታዊ የሚባሉ የዜጎች ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች መከበር ከማንኛውም አገር የሚጠበቁ እሴቶች እየሆኑ መጥተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን ለማስከበር ያደረገው ያላቋረጠ ትግል የአምባ-ገነኖች ሥርዓትን አዙሪት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሰብሮ አስተማማኝ መረጋጋትና ሰላምን ለማግኘትና በፈቀደውና በመረጠው መንግሥት መተዳደር የሚያስችለው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት መሆን አላስቻለውም፡፡ አሁንም እንዳለፉት ጊዚያት የመብቱ ባለቤት አይደለም፡፡ ትግሉን ግን አላቆመም፤ አያቆምም፡፡

ለዚኽ የመብት እጦት ዋናው ምክንያት ሕዝባችንን በተገቢው መልክ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያሸጋግረው ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት ማድረግ እንዳይችል በመደረጉና በየጊዜው ብልጭ ያሉ ተሩዎች ቶሎ እንዲከስሙ እየተደረገ ዕድሉን በመነፈጉ ነው፡፡

አንድንድ ወገኖች ምናልባት በደርግ ጊዜም ሆነ በሕወሓት/ኢሕአዴግ የተደረጉትን "የሽግግር" ክስተቶች ሽግግር እንደተደረገ አድርገው ሊያቀርቡት ይችሉ ይሆናል፡፡ በእርግጥ ወታደራዊ ደርግ ከጊዚያዊ ወታደራዊ መንግሥትነት ወደ ኢሠፓዊ መንግሥትነት፣ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በጠበበ መሠረትና ይኽ ነው የሚባል ሕዝባዊ አመኔታም ይሁን ተቀባይነት ከሌለው የሽግግር መንግሥትነት እንበለ ብሔራዊ ራእይ ያው እንደጠበበ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥትነት እራሣእቸውን አሸጋግረዋል፡፡ ሆኖም ግን በደርግም ሆነ በሕወሓት/ኢሕአዴግ የታየው "ሽግግር" ሁለቱም ድርጅታዊ ባኅሪያቸው፣ አወቃቀራቸው፣ ይዘታቸውና መሠረታዊ አቋማቸው ሳይለወጥ፣ የሕዝቡን ፍላጎትና ይሁንታ ባልጠበቀና በተናጠል እራሣቸውን ወደ ቋሚ መንግሥትነት የቀየሩበት ክንዋኔ ነው፡፡ እርግጥ ይኽንንም ለማድረግ ሕዝቡ ምረጥ ተብሏል፡፡ ምርጫዎቹ ግን ሕዝቡ ይመሩኛል፤ ያስተዳድሩኛል፣ ችግሬን ይፈቱልኛል ብሎ ያመነባቸውን መምረጥ ያልቻለባቸው፣ ነፃ ሆኖ ያልተሳተፈባቸውና በትእዛዝ የተፈፀሙ ምርጫ የሌላቸው ምርጫዎች ነበሩ፡፡

ዴሞክራሲያዊ ሽግግር የምንለው እንደ መንግሥቱ ኃ/ማርያም/ደርግና መለስ ዜናዊ/ሕወሓት ዓይነቱን ግለሰቦችንም ይሁን ድርጅቶችን ከጊዚያዊ መንግሥትነት ወደ ቋሚ መንግሥትነት የሚያስተላልፈውን ዓይነት የቅብብሎሽ ኩኔት ሣይሆን ሕዝብን ከእንበለ-ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያሸጋግር ሂደትን ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ የተወሳሰቡ ችግሮች ያሉባቸው አገሮች ችግሮቻቸውን በሰከነ መንገድ ለማስተናገድና በዘለቄታዊነት ለመፍታት እንዲችሉ አግላይነት የሌለውና ሁሉን ያቀፈ፣ እራቅ አድርጎ ያየ፣ ሕዝቡን ያቀፈና በቀጥታ ያሳተፈ፣ ግልፅነትና ተአማኒነት ያለው ብሔራዊ እርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደትን መከተልና መፈፀም እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉ ከአፄ ኃይለ-ሥላሴ ዘመነ-መንግሥት ጀምሮ አሁን እስካለው ሕወሓት/ኢሕአዴግ በልዩ ልዩ ደረጃ ምርጫዎች ተካሂደዋል፡፡ አንዳቸውም ግን ሕዝባችንን የሥልጣኑ ባለቤት ሊያደረጉ፣ ኅብረተሰባችንን አንቆ ከያዘው የአምባ-ገነኖች አዙሪት ሊያላቅቁትና ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊያሸጋግሩት አልቻሉም፡፡ ያም በመሆኑ አገራችን አስተማማኝ መረጋጋትንም ይሁን ሕዝባችን ከተመላላሽ የችግር አዙሪት ጥንውት ሊላቀቅና የብልፅግና ጎዳናን ሊከተል አልቻለም፡፡

በአንድ አገር ምርጫ መደረጉ ብቻውን የዴሞክራሲ ሥርዓት መኖርንም ይሁን የሕዝብ መብት መረጋገጥን አያረጋግጥም፡፡ በአገራችን ባለፉት ሦስት መንግሥታት የተደረጉ ምርጫዎች ውጤታቸው ተመሣሣይ ነው፡፡ ያም በጊዜው ያለውን መንግሥት በሥልጣን ላይ ማቆየት ነው፡፡ ይኽም የሆነበት ምክንያት ግልፅ ነው፡፡ የተደረጉ ምርጫዎች ዝግጅት፣

*ሂደትና ክንዋኔ ቁጥጥር ሙሉ በሙሉ በነዚሁ የመንግሥት ሥልጣን በያዙ ክፍሎች ሥር ስለሆነ ነው።*

*በአፄ ኃይለ-ሥላሴ ዘመነ-መንግሥት የተደረጉ የሕዝብ ተወካዮች ምርጫ ዓላማው የሕዝቡን መብት የተሻለ ለማስከበር በማሰብ ሣይሆን በጊዜው በነበረው ሕገ-መንግሥት "ዘውዱ ለዘለዓለም ከአፄ ኃይለ-ሥላሴ ዘር ሳይወጣ ይኖራል" ተብሎ በተደነገገው መሠረት የንጉሠ-ነገሥቱን መንግሥት ቀጣይነት የበለጠ ለማረጋገጥ እንደነበር ሁሉ፤ በወታደራዊ ደርግ (ኢሠፓ) የተደረገውም ምርጫ እንዲሁ ሕዝብን የሥልጣኑ ባለቤት ለማድረግ ሣይሆን "የወዝ-አደሩን" አምባ-ገነንነት ለማረጋገጥ ነበር። በሕወሓት በሚመራው ኢሕአዴግ ሥር የተደረጉ ምርጫዎችም እንዲሁ በተራቸው በአብዛኛው ከለጋሽ አገሮች እርዳታን ለማስገኘት ያኽል ብቻ ታስበው በዴሞክራሲ ስም የተከናወኑ ሆኖም አጠቃላይ ዓላማው ድርጅቱ ቆምኩለት የሚለውን "የዓብዮታዊ ዴሞክራሲ" ርዕዮት በተግባር ለመተርጎም እንዲችልና ሕዝብን ከፋፍሎ በሥልጣን እስከወዲያኛው ለመቆየት የተጠቀመበት ሕጋዊ ጭምብል ነው። ስለሆነም በሦስቱም መንግሥታት ሥር የተደረጉ ምርጫዎች ዓላማቸው አንድና አንድ ብቻ፣ ማለትም በሥልጣን ተደላድሎ ለመቆየት ስለሆነ ይኸንን ለማረጋገጥ የምርጫውን ውጤት የሚወስነውን ሂደት ከመጀመሪያ እስከ-መጨረሻ ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠሩታል። የምርጫው ውጤት ሕዝብ ከነሱ ሌላ ሊመርጥ እንደሚችል፣ ውጤቱ እነሱን ከሥልጣን ሲያገልልና በተቃዋሚነት ደረጃ ሊያስቀምጣቸውና "ከውጭ ሆኖ ተመልካች" ሊያደርጋቸው እንደሚችል ጨርሶ አይታያቸውም፣ ከነሱ ሌላ ለሕዝብ አማራጭ ሊሆን ይችላል ብለው አያስቡም፣ አይፈቅዱምም!*

*አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ከምርጫ፣ በተለይም ደግሞ አምባ-ገነና ኢ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዞች እራሣቸው ለራሣቸው ጥቅምና ግብ አስበውና አስልተው ከሚያዘጋጁት ምርጫ ዴሞክራሲ ሊወለድ እንደማይችል ነው። ከዴሞክራሲ ግን ትክክለኛና ሕዝብ ያመነበት እውነተኛ ለውጥ-አስገኝና ሕዝቡን በእርግጥ የሥልጣኑ ባለቤት የሚያደርግ ምርጫ ማድረግ ይቻላል። ይኽ ደግሞ የዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት መኖርን የግድ ይላል።*

*ማንኛውም ምርጫ የሥልጣን ብቸኛ ባለቤት የሆነው ሕዝብ የፈቀደውን የመንግሥት ሥርዓትና መንግሥት በመሰየም በመረጣቸው ሰዎችና ድርጅት (ፓርቲ) መተዳደር እንዲችል የሚደረግ ምርጫ ዓለም-አቀፍ የምርጫ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርበታል የሚል አቋም በተቃዋሚው በኩል ሲገፋ መቆየቱና ከዥሮው ፓርቲም ሳይቀር የተባሉትን መሥፈርቶች አሟላለሁ እያለ ሲመፃደቅ መደመጡ ይታወቃል።*

*ለመሆኑ ዓለም-አቀፍ መሥፈርቶች ስንል ምን ማለታችን ነው?*
*በቅድሚያ ማንኛውም ምርጫ ነፃ፣ ፍትኃዊና ርቱዓዊ እንዲሆን የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላት አለበት።*

*ሀ. የምርጫው አዘጋጅና አስፈፃሚ አካል ብቃትና ችሎታው ባላቸው ሙያተኞች የሚመራ፣ ገለልተኛና ከተወዳዳሪዎች (ተፎካካሪዎች) ተናጠል ጫናናና ተፅእኖ ፍፁም ነፃ መሆን፣ ሁሉንም ተወዳዳሪዎች በእኩል ማየትና ማስተዳደር የሚችል መሆን ይኖርበታል።*

*ለ. የሕግ የበላይነት በተረጋገጠበት ሁኔታ ሕዝብ ያለምንም መሳቀቅ፣ ፍራቻና ጫና ለፈቀደውና መልካም ይሠራልኛል ብሎ ላሰበውና ላመነው ሰው ወይም ድርጅት ድምፁን መስጠት መቻል አለበት።*

*ሐ. ማንኛውም መራጭ ዜጋ የሚሰጠው ድምፅ ምሥጢራዊነት መከበር፣ የሰጠው ድምፅም በትክክል የመቆጠርና እኩል ዋጋ እንዲኖረው ያስፈልጋል።*

*መ. የምርጫ ተወዳዳሪዎች ለአገርና ለሕዝብ ያላቸውን ራእይና የተሻለ ነው ብለው የሚያቀርቡትን አማራጭ ያለ ጫናና ተፅዕኖ በነፃነት በቀጥታና በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት ለሕዝብ የማቅረብና ከሕዝብ ጋርም የመወያየት መብታቸው የተከበረና በተግባር የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡፡*

*የ*1948 *ዓ/ም ዓለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብት አዋጅ የምርጫ መብትን በተመለከተ በአንቀፅ* 21 *የተጠቀሰውና በ*1966 *ዓ/ም የወጣው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት በአንቀፅ* 25 *በተጠናከረው መሠረት፤ ማንኛውም ዜጋ አጥጋቢና ሕጋዊ ተቀባይነት ባለው ምክንያት ካልሆነ በስተቀር፤*

*ሀ*) *በቀጥታ ወይም በነፃ ፍላጎቱና ምርጫው በሚወክላቸው ሰዎች አማካይነት በአገሩ አስተዳደርና የፖለቲካ ሕይወት ተሳታፊ የመሆን፣*

*ለ*) *በየተወሰነ ጊዜ በሚደረግ፣ በምስጢር ተፈፃሚ በሚሆን፣ አንድ-ሰው-አንድ-ድምፅ በሚለው መርኅና የመራጩን ፍላጎት በትክክል በሚያንፀባርቅ ምርጫ ተሣታፊ በመሆን የመምረጥና የመመረጥ፣*

*ሐ*) *አገሪቱ በምትሰጣቸው መገልገያዎች እኩል ተጠቃሚ የመሆን፣*

*ሙሉ መብት እንደሚኖረው ያረጋግጣል፡፡*

*እነዚኽ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ግን እርባና የሚኖራቸው የምርጫ ሂደቱ ትርጉም እንዲኖረው ለማስቻል በምርጫው ወቅት የሚደረገው "የውድድር ሂደት መብት" ተብለው የተጠቀሱት መብቶች ሲከበሩና ተፈፃሚ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡*

*በዚኽ ረገድ አንቀፅ* 19 *እንዲህ ይላል፤*
*"ማንኛውም ዜጋ የማሰብ፣ ያለ ምንም መሣቀቅና ጣልቃ-ገብነት አሳቡን በፅሑፍም ይሁን በቃል፣ በሥዕልም ይሁን በምልክት፣ ባመቸውና በመረጠው መንገድ በነፃነት የመግለፅ፣ የማወቅ፣ ወሰን ሳይገድበው መረጃ የመጠየቅና የማግኘት ሙሉ መብት አለው፡፡ ይኽ ሲሆን በዜጎች በኩል ደግሞ የሌሎችን መብትና ክብር የመጠበቅ፣ ብሔራዊና ማኅበረሰባዊ ፀጥታንና ደኅንነትን የማክበር ግዴታ ..." እንዳለ ይገነዘቧል፡፡*

*አንቀፅ* 21 *የዜጎችን በሰላማዊ መንገድ የመሰባሰብ መብትን ሲያረጋግጥ፣ አንቀፅ* 22 *ዜጎች ልዩ ልዩ መብቶቻቸውን ለማስከበርና ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ በሚረዳቸው መልክ የመደራጀት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡*

*ሕዝብ በነፃ ፈቃዱና ፍላጎቱ ይሆነኛል የሚለውን መንግሥት የመምረጥ መብትን በተመለከተ ስለ ሰዎችና ሕዝቦች መብቶች የወጣው የአፍሪቃ አንድነት ቻርተር፣ የአሜሪካና የአውሮጳ የሰብዓዊ መብት ኮንቬንሽኖች ተመሣሣይ ድንጋጌዎችን ያስቀምጣሉ፡፡*

*ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ ወዲኽም ሰፋ ያለ ሕዝባዊ ተሳትፎን ያገኙና የተሻለ ተስፋ ተጥሎባቸው የነበሩ ምርጫዎች ተከናውነዋል፡፡ ይሁንናም አንዳቸውም ሕዝባችንን ለሥልጣኑ የሚያበቁና ፍላጎቱን ያሟሉ አልነበሩም፡፡ ከሁሉም በላይ ይበልጥ ከፍተኛ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው ምርጫ በ፲፱፻፺፯* (2005) *የተካሄደው እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ ተስፋ የተደረገበትም ምክንያት አጠቃላይ የፖለቲካ ምኅዳሩ ቀደም ሲል ከነበሩት ሁኔታዎች የተሻለ ሰፋ ያለበትና ያም በመሆኑ ሕዝባችን ሲመኘው የነበረውንና የተዋደቀበትን በድምፁ የፈለጋቸውን ወኪሎቹንና መሪዎቹን የመምረጥና በመረጣቸውም የመተዳደር መሠረታዊ መብቱን ለማስከበር የሚችልበት የተሻለ ሁኔታ አለ በሚል እንደነበር ግልፅ ነው፡፡*

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከቀዝቃዛው ጦርነት ወዲኽ በሰፈነው አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ በዓለም ዙሪያ ያሉ መንግሥታት ሕጋዊ መሠረታቸውን ሕዝብን በምርጫ መማሳተፍ በሚደረግ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ላይ እንዲሆን እየተለመደ በመምጣቱና ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡም ይኽንን እንደ መመዘኛ መወሰዱ አምባ-ገነን መሪዎች ሕዝብን እንደፈለጉት ረግጠውና ቀጥቅጠው የመግዛት ባኅሪያቸውን ቢያንስ ላይ ላዩን መቀየር እየተገደዱ የመጡበት፣ ይኽም ለፍትኀዊ ሥርዓት ለሚታገሉ ወገኖች አንፃራዊ በሆነ መልኩ ሻል ያለ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታን ማስፈን በመቻሉ የሕዝብ መብቶች እንዲከበሩ የሚያደርጉትን ትግል እንዳበረታታ ግልፅ ነው፡፡

በአገራችንም ያለ ውጭ እርዳታ መኖር የማይችለው የአቶ መለስ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ከዚኽ ክስተት ሊያመልጥ አልቻለም፡፡ ስለሆነም በአቶ መለስ የሚመራው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት የውጭ እርዳታን ለማስገኛና ለታይታ ያኽል ዴሞክራሲ አለ ለማሰኘት ይረዳሉ ብሎ በማሰብና ዴሞክራት ሆኖ ለመቅረብ በማስላት ቅድመ-ምርጫ ግንቦት ዘጠና-ሰባት በመቅኑን ሊባል በሚችል ሁኔታና ቁጥጥር በበዛበት መልክም ይሁን እንጂ በአገራችን ከዚያ በፊት ከነበረው በተሻለ የፖለቲካ ምኅዳሩን ገርበብ ማድረግ ነበረበት፡፡ ያ አንፃራዊ ክፍተት በመፈጠሩም ከአገዛዙ የሚደርስባቸውን ጫና ሁሉ እየተቋቋሙ፣ እየወደቁም እየተነሱም አንዳንድ ለዴሞክራሲው ሂደት ቁልፍ ሚና የሚጫዎቱ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ማቆጥቆጥ ችልለዋል፡፡ በዚኽ ረገድ በተለይ የኅትመት ስርጭቱ (ነፃው ፕረስ) በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡

የፖለቲካ ድርጅቶችም ከተጠናዎታቸው የተናጠል ጉዞ አባዜ እየተላቀቁ በመጀመሪያ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ከዚያም በቅንጅት ዙሪያ መሰባሰብ በመቻላቸው፣ የትግል ስልታቸውንም ሕዝብን ሊያሰባስብ በሚችል መልክ እያሾሩ በመሄዳቸው፣ ለአገራችን ሕወሓት/ኢሕአዴግ ከሚከተለው ፖሊሲ የተሻሉ ናቸው የሚሏቸውን አማራጮችም ለሕዝብ ማቅረብ በመቻላቸው፣ ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡም አገዛዙ አቅጣጫውን እንዲስት ያደረገውና ያወናገረው የዴሞክራሲ ሂደት በትክክል እንዲሄድ ለማስቻል የሚደረገው ምርጫ ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን ውትዎታቸውን በመጨመራቸው፣ ወዘተ... ሕዝባችን በተቃዋሚው ላይ የተሻለ አመኔታን እየጣለ፣ በአገዛዙ ላይ ያለውን ድክመት የተሻለ እየተረዳ፣ ለተቃዋሚው ያለውን ድጋፍ በገሃድ ለመግለፅ እየተደፋፈረና ለለውጥ ያለውን ዝግጁነትና ጉጉት እያሳየ በመጣበት ሁኔታ ነው ምርጫ ዘጠና ሰባት የተካሄደው፡፡ በዚያም ታሪካዊ ምርጫ ከመራጩ ሕዝብ ሰማንያ ሦስት ከመቶ የሚሆነው ተሣታፊ በመሆን ኃይሉንና ቁርጠኛነቱን ብቻ ሣይሆን ብስለቱን፣ ፍላጎቱንና ውሳኔውን በማያሻማ ሁኔታ ለዓለም አሳውቋል፡፡

ይሁንናም የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነትና ወሳኝነት ከመጤፍ የማይቆጥሩትና ለሕዝብ ከበሬታ የሌላቸው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ኃላፊነት በጎደለውና በዕብሪት መንፈስ ጥሬ ጉልበት በመጠቀም በጠራራ ፀሐይ ድምፁን ቀሙት፣ ቂም-በቀል ያዘለ ዘመቻቸውን አወጁበት፣ የግፍ ዱላቸውን አሳረፉበት፣ ለሥልጣናቸው ሲሉ ማመን በሚያዳግት ሁኔታ በራሣቸው ሕዝብ ላይ ሽብራቸውን አጧጧፉበት፡፡

በዚያም እነ አቶ መለስ ዳግም "የተሰላ አደጋን" ላለመጋበዝ ምለው ተነሱ፡፡ ለዴሞክራሲ ሂደቱ ግንባታ አስፈላጊ በሆኑትና ምርጫ ዘጠና-ሰባት ይዞት የወጣውን ውጤት ይዞ እንዲወጣ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉትን እንደ ነፃው ፕረስ የመሣሰሉትን ተቋማት ድምጥማጣቸውን የማጥፋት አረመኔዓዊ እርማጃዎቻቸውን በሁሉም አቅጣጫ አጧጧፉ፡፡

በአጠቃላይ ስለ ምርጫ ሲነገር ምርጫው በሚካሄድበት ቀን ስለሚከናወነውና ስለሚገኘው ውጤት ብቻ የሚወሰድ ጉዳይ አይደለም፡፡ ምርጫ ሂደት ነው፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ምርጫ ተሣታፊውን ሕዝብ በሚጠቅም ወይም በማይጠቅም፣ ሕዝቡ በፈለገው ወይም ባልፈለገው መንገድ ሊደመደም መቻል አለመቻሉ የሚወሰነው ከምርጫው ቀን

በፊት ባሉት ወራት ተወዳዳሪ ክፍሎች በመራጩ ሕዝብ ፊትና ከመራጩ ሕዝብ ጋር ማድረግ የቻሉት ወይም ያልቻሉት ቅርርብ፣ አሳቦቻቸውንና አማራጮቻቸውን በተገቢ ማስተላለፍ መቻል አለመቻል፣ ሕዝቡም በእውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔውን መስጠት እንዲችል ከተፎካካሪዎቹ የሚቀርቡ አማራጮችን በትክክልና በቀጥታ ማወቅ የሚችለበት ሁኔታ በመኖሩ ወይም ባለመኖሩ ስለሆነ የአንድ ምርጫ የሕዝብን ፍላጎት ማርካት አለማርካቱ ወይም ነፃ መሆን አለመሆኑ የሚለካው በምርጫው ዝግጅትና ሂደት ነው:: ሕዝብ ሃቀኛ ምርጫ አደረገ የሚባለው መራጩ ሕዝብ ከልዩ ልዩ ተወዳዳሪዎች የተያይዩ አማራጮች ሲቀርቡለት እንጂ አንድን ዓይነት አቋምና ፖሊሲ በተለያዩ ሰዎች ስለቀረበለት አይደለም::

አንድ ሕዝባዊ ምርጫ የሚወሰነውና ምን ዓይነት ምርጫ መሆኑ የሚለካው ምርጫው በሚካሄድበት ቀን በሚደረግ ክንዋኔ ብቻ አይደለም:: አንድን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ የሚያደርገው በምርጫው ቀን በሚከናወነው የድምፅ አሰጣጥና አፈፃፀም በነጠላው ሣይሆን ተወዳዳሪዎች ያላቸውን አማራጭ በነፃነትና ያለምንም ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ሊመርጣቸው በሚፈልጉት ሕዝብ መኻል እንደ ልብ ተንቀሳቅሰው በአካል በመገኘትም ሆነ በተለያዩ መንገዶችና ዘዴዎች ማሳዎቅ ሲችሉ፣ መራጩ ሕዝብም ያለ መሣቀቅና ፍራቻ ጥያቄ እየጠየቀም ይሁን አሳቡን በነፃ በመግለፅ በሚደረገው የምርጫ ውድድር ሂደት እንስቃሴ ቀጥተኛ ተሣታፊ ሲሆን፣ ወዘተ.. ነው::

ምርጫ ትርጉም እንዲኖረው የመወዳደሪያ መስኩ ለሁሉም የምርጫ ተፎካካሪዎች፣ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያለ ይሁን አይሁን፣ ድርጅት ይሁን ግለሰብ እኩል ክፍት እንዲሆንና በአንድ መልኩ ይሁን በሌላ ምንም ዓይነት አድልዖ የሌለበት ሁኔታ እንዲኖር ያስፈልጋል::

እንደሚታወቀው ሁሉ በኢትዮጵያችን እንደሚታየው የአገርን መከላከያ ኃይል፣ የፖለስና የፀጥታ ክፍል፣ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት፣ የመንግሥት ግምጃ ቤት፣ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፣ አልፎም አጠቃላይ የአገር መሬት፣ ወዘተ.. በምርጫ ከሚወዳደሩት ክፍሎች መኻል በአንደኛው ሙሉ ቁጥጥር ሥር በዋለበት ሁኔታ ነፃና ፍትኃዊ ምርጫ ሊደረግ ከቶውንም አይቻልም:: አንድ ምርጫ ነፃ መሆኑ የሚለካው ደግሞ ሕዝብ የፖለቲካ ፍላጎቱን ያለ አንዳች ጫናና ጣልቃ-ገብነት መግለፅ የሚችልበትና ሙሉ በሙሉ ማንፀባረቅ የሚችልበት ሁኔታ በመኖሩ ወይም ባለመኖሩ ነው::

በአገራችን የሚደረግ ምርጫ ዓለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብት አዋጅም ሆነ የራሱ የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት ላይ የተደነገጉ የምርጫ ሕግጋት እየተጣሱና አስፈላጊ መስፈርቶች ሳይሟሉ የሚደረግ እስከሆነ ድረስ ምርጫው ይስሙላዊ ከመሆን አያልፍም::

በዴሞክራሲ ሥርዓት የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ሕዝብ ነው፣ ሉዓላዊነት የሕዝብ ነው:: ሕዝብ ለልዩ ልዩ ኃላፊነት የሚመርጣቸው ሰዎች የመረጣቸውን ሕዝብ በተመረጡበት ኃላፊነት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚያገለግሉ እንጂ የፈለጋቸውን እንዳሻቸው በሕዝብ ላይ ለማድረግ አይደለም::

ሕዝብ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑን በተግባር የሚተረጉመው 'አንድ-ሰው-አንድ-ድምፅ' በሚለው መርኅ መሠረት ዜጎች ፍላጎታቸውን ያሟላል፣ መብታቸውን ያስከብራል ላሉት ሰው ወይም ድርጅት ድምፃቸውን በነፃነትና በምሥጢር በመስጠት፣ የሰጡት ድምፅም እኩል ክብደት ተሰጥቶትና በትክክል ተቆጥሮ ውጤቱ በተግባር ሲረጋገጥ ብቻ ነው::

ከአሁን በፊት ድርጅታችን ድኅረ-ምርጫ ዘጠና ሰባት የተከሰተውን በሚከተለው መልክ አቅርቦት ነበር::

*"በአጠቃላይ ሲታይ በሚከተሉት ምክንያቶች ከግንቦት ዘጠና-ሰባት ታሪካዊ ኩኔት ከተቃዋሚው ክፍል ይበልጥ ገዥው ፓርቲ ብዙ ትምሕርት ቀስሟል ማለት ይቻላል።*

*1. ከደርግ አገዛዝ መወገድ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በገዥው ፓርቲ ይሁንታና ድጋፍ ባይሆንም በተፈጠረው አንፃራዊ ክፍተት በመጠቀም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ተቋማት በመንግሥት በኩል የሚደረግባቸውን ከፍተኛ ጫና ሁሉ ተቋቁመው ማቆጥቆጣቸው ይታወቃል። በዚህ ረገድ በተለይም የነፃው ፕረስ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። በዚህ ክፍል (ነፃው ጎትመትና ስርጭት- ፕረስ) የተሰለፉ ቆራጥ ዜጎች እየታሰሩ፣ እየተፈቱ፣ አይቀጡ ቅጣት እየተቀጡ፣ እየወደቁና እየተነሱ ባደረጉት ትግል ሕዝባችን በአገራችን የቆየውን የመንግሥት ሥልጣን በያዘ ክፍል ላይ ግልጽ ወቀሳና ትችት የማድረግን "የነውርነት" ጭምብል ቀስ በቀስ የገፈፈና በውስጡ የተዳፈነ የለውጥ ፍላጎቱንና ስሜቱን አንገቱን ቀና አድርጎ በይፋ እንዲገልጽ በማስቻሉ ለግንቦት የሕዝብ ድሎች ቀጥተኛ አስተዋጽዖ እንዳደረገ ገዥው ክፍል በሚገባ ተረድቷል።*

*2. ሕዝቡ ድምፁን በነፃ ለመግለጽ ዕድሉን ካገኘ ማንም በሚያደርገው የተለመደ የጥቅም ድለላም ሆነ ማስፈራራት፣ አልፎም እስራት፣ ግርፋትና ግድያ፣ በተለይም ደግሞ ገለልተኛ ታዛቢ ባለበት ሁኔታ፣ በብቸኝነት የሚሰጥን ድምፅ ሊያስቀይር ወይም ሊለውጥ እንደማይቻል የኢሕአዴግ ቁንጮዎች በደንብ ተገንዝበዋል።*

*3. እንዲሁም የዜጎችን ቀልብ በሳበ መልክ ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ የተሻሉ አማራጮችን ለሕዝብ የሚያቀርብ የተደራጀ* ***የአንድነት ኃይል*** *ዕድሉን አግኝቶ ከተሰለፈ ሕዝብ አመኔታውን ሊጥልበት፣ ሊከተለውና ሊደግፈው ብቻ ሳይሆን አብሮት ሊቆምና መስዋዕት ሊሆን እንደሚችልና እንደተዘጋጀ አገዛዙ ጠንቅቆ ተረድቷል።*

*4. እ.ኢ.አ. ከመስከረም አሥራ-አንድ ሁለት ሽህ አንድ ዓ/ም ወዲህ በተቀየረው የዓለም ፖለቲካ እንዲሁም በአካባቢው የዋለለና አሳሳቢ የውጥረት ሁኔታ ምክንያት ከደጋፊዎቹና ከእርዳታ-ለጋሽ አገሮች በኩል አንፃራዊ ወታደራዊ ጥንካሬና ለሚጠየቀው ትብብር ሁሉ ዝግጁና ታዛዥ እስከሆነ ድረስ እንዲሁም ተቃዋሚው በተበተነ መልክ እስከቀጠለ ድረስ በራሱ ሕዝብ ላይ በሚወስዳቸው እርምጃዎች እንኳን ግንኙነትና እርዳታ ማቋረጥ ብዙ ጫናና ይፋዊ ኩነና እንደማይደርስበት አገዛዙ በሚገባ አውቋል።*

*ስለሆነም ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ፤ ምናልባትም የአመራር ለውጥ ወይም አሁን ባሉት መሪዎች ዘንድ እጅግ ከተአምር የሚቆጠር መሠረታዊ፣ የምርና ከልብ የተደረገ የአስተሳሰብ ለውጥ ከሌለ በስተቀር፤ ከአሁን በኋላ ያ በአቶ መለስ አነጋገር "የተሰላ ምናልባታዊ አደጋ" (Calculated risk) የሚወሰድበት ሁኔታ ዳግም ተመልሶ ይመጣል የሚል ግምት ሊኖር አይችልም። ገዥው ፓርቲ ከግንቦት ሰባት ዘጠና-ሰባት ማግስት ጀምሮ በአንድ በኩል ያ ሁኔታ እንዳይደገም እነዛን ተቋማት እንዳልነበሩ ለማድረግ፤ ሕዝቡም በራሱ ተመክቶ፣ በተቃዋሚ ድርጅቶች ተማምኖ፣ አንገቱን ቀና አድርጎና በድምፁ ኃይል የሚፈልገውን ለውጥ ለማምጣት እምነቱና ድፍረቱ እንዳይኖረው ቅስሙ እንዲሰበር በማድረግ፣ በሌላ በኩል ተቃዋሚው በማንኛውም የአገሪቱ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የሚኖረው ሚና እራሱ ገዥው ፓርቲ ባሰመረለት ተቃዋሚ አለ ለማሰኘት ለይስሙላ ያኽል ከአጃቢነት ባልተለዬ ቀጭን መሥመር ብቻ እንዲወሰንና በማንኛውም ምርጫ በተባለ ጉድ ከላይ እስከ ታች እሱና ተባባሪዎቹ ብቻ "በአቸናፊነት" የሚሰየሙበት ሁኔታ እንዲመቻች ለማድረግ ያለ የሌለ ኃይሉን በማረባረብ ላይ ተሰማርቶ ቆይቷል። ውጤቱም ከስሌቱ ውጭ እንዳልሆነ በአጠቃላይ ከምርጫ ዘጠና-ሰባት ወዲህ በተከተላቸው ሂደቶችና በተለይ በቅርቡ በተደረገው "የማሚያ፣ የወረዳና የቀበሌ" ምርጫ በማያሻማ ሁኔታ በደንብና በግልጽ ታይቷል።*

*በአጠቃላይ ሲታይ ገዥው ፓርቲ በተለይ ከምርጫ ዘጠና-ሰባት ወዲህ የሚያደርጋቸው ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎች የሚያመላክቱት በአገሪቱ ላይ የአንድ ፓርቲ ብቸኛ የበላይነት*

*በሚያወላዳ መልኩ እንዲደላደል የሚያደርግና የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት ቅታው ጠፍቶ የአገሪቱ አጠቃላይ ዕድል በኢሕአዴግ አልፎም በአንድ ግለሰብ ብቻ እንዲወሰን የሚያደርግ ነው። ይኽ የአንድ ፓርቲን ሁለንተናዊ የበላይነት በአገሪቱ ላይ ለማስፈን የሚደረግ ከፍተኛ ጥረትም እውነተኛ የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት ግንባታ ዕድሉ በጣም እየጠበበ እንደሚሄድና ከናካቴው ለማክሰም አገዛዙ ለሚያደርገው ቁርጠኛ ጥረት ጠንካራ አመላካች ነው።"*

ምርጫ ዘጠና-ሰባት በተለይ ቀደም-ሲል በአገራችን ከተካሄዱ ምርጫዎች ጋር ሲነፃር ከሞላ ጎደል ነፃ ነበር ማለት ይቻላል። ሕዝብም ድምፁን ሊሰጥባቸው የሚችል አማራጮችና ድምፁን በእምነት የሰጣቸው ድርጅቶች ቀርበውለት ነበር። በአሁኑ ጊዜ በገዥው ፓርቲ በኩል ይሁን በተቃዋሚው ክፍል፣ ሕዝብ በምርጫ ላይ ያለው ተስፋ ይሁን በዴሞክራሲ እሴቶች በኩል፣ ወዘተ. ያለው ሁኔታ በብዙ ረገድ ተቀይሯል። ያልተለወጠው ሕዝባች ለዴሞክራሲና ለመብቶቹ መከበር ያለው የተቃጠለና የታመቀ ፍላጎት ብቻ ነው።

ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ የበርካታ ኢትዮጵያውያን ጭንቀትና ትኩረት የሚቀጥለው ምርጫ ምን ይዞ ይወጣ ይሆን የሚል አይደለም። ያማ ከወዲሁ አስቀድሞ የታወቀ ነው። በድርጅታችን እምነት በቀጣዩ አጠቃላይ ምርጫ (ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት) የሚከተሉት ክስተቶች እንደ አይቀሬ እውነታ ሊወሰዱ ይችላሉ።

1. በአገሪቱ የተፈጥሮም ይሁን ሌላ (በገዥው ፓርቲ ቁንጮዎች ላይ በሚደርስ አደጋም ይሁን ሌላ ትርምስ) እጅግ የከፋ ችግር ምክንያት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያሳውጅ አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በግንቦት ሁለት-ሽህ-ሁለት ይደረጋል የተባለው ምርጫ ይካሄዳል።

2. ሕዝብ በምርጫው ይሣተፋል። የሕዝቡ ተሣትፎ ግን በውዴታ ወይም የተሻለ ለውጥ ያመጣል በሚል ሣይሆን "<u>ላለመምረጥ" (ላለመሣተፍ) ምርጫ ስለማይኖረው ነው።</u> በቀጭን ትዕዛዝ የሚፈፀም ነው። የመንግሥት ጢሰኛ የሆነው ገበሬ እርሻውን፣ ነግዶ የሚተዳደረው ወገን የንግድ ፈቃዱን፣ ሠራተኛው ሥራውን፣ ተማሪው የወደፊት የትምሕርት ዕድሉን፣ ወዘተ.. ላለማጣት ብቻ በዚኽ ምርጫ የለሽ ምርጫ መሣተፍ ይገደዳል።

3. የፖለቲካ ድርጅቶች በምርጫው ይሣተፋሉ። ሁሉም በምርጫ የሚሣተፉ ድርጅቶች ግን ወደውም ሆነ የተሻለ ውጤት እናመጣለን ብለው አይደለም። የአገዛዙ አገልጋይ የሆነው "ምርጫ ቦርድ" የተባለ አካል ባወጣው ደንብ መሠረት እያንዳንዱ ሕጋዊ ሆኖ የተመዘገበ ድርጅት በአገሪቱ በሚደረጉ ምርጫዎች ከአንድ ጊዜ በላይ አልሳተፍም ማለት አይችልም። ልክ በምርጫ ያልተሣተፈ (በግልፅ ለተቃዋሚ የመረጠማ ይባስ ነው!) ሠራተኛ የሥራ ፈቃዱን፣ ገበሬው መሬቱን እንደሚቀማ ሁሉ ከአንድ ጊዜ በላይ በምርጫ ያልተሣተፈ ድርጅት የተሰጠውን ፈቃድ ተነጥቆ "ሕገ-ወጥ" ስለሚሆን ባለፈው "የወረዳ፣ የዞንና ማሟያ፡ በተባለው ምርጫ ተሣታፊ ያልነበሩ ድርጅቶች "ሕጋዊ" ሆኖ መቀጠል እስከፈለጉ ድረስ በቀጣዩ ምርጫ (ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት) የመሣተፍ ግዴታ ይኖርባቸዋል።

4. ገዥው ፓርቲ ባለፈው ምርጫ በዓለም ፊት እራቁቱን የቀረበትን ውርደትና ኪሣራ ውስጥ የገባበትን አጉል መተማመን ይዞ ሕዝብ አመኔታውን የጣለባቸውና እውነተኛ አማራጭ ሆነው የሚቀርቡ ድርጅቶች (በተለይም ጠንከር ያለ የአንድነት ኃይሎች) በምርጫው እንዳይሣተፉ ከወዲሁ ሁኔታውን እንደሚያመቻች ግልፅ ነው። በድርጅቶች መኻል አለመተማመን እንዲሰፍን፣ እርስ-በርስ መባላት እንዲኖርና ተሣታፊ ከሆኑም ተበትነውና አቅመ-ደካማ ሆነው እንዲገኙ ይጥራል። በተቃዋሚው ጎራ አሁን የሚታየው የሚያረጋግጠውም ይኽንኑ ነው። ስለዚህ ተቃዋሚው የሚገኝበትን የመበታተን አሳፋሪ ይዞታውን ካላረመ በምርጫው የሚሳተፈው በአንድ በኩል ሕወሓት/ኢሕአዴግ በሌላ በኩል ተቃዋሚው ሆኖ ሣይሆን ሕወሓት/ኢሕአዴግ ከብዙ የተበታተኑ ድርጅቶች ጋር ይሆናል ማለት ነው።

በተለይ በቅርቡ የወጣውን “ፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ” መሠረት በማድረግ በአገር ውስጥ ያሉና ከአገር ውጭ የሚገኙ ድርጅቶች ሊኖራቸው የሚችለውንና የሚገባውን የትግል ትሥሥር በልዩ ልዩ መንገድ ለመበጠስና አልፎም በአገር ውስጥ “ሕጋዊ” ኀልውና ይዘው የሚንቀሣቀሱ ድርጅቶች በውጭ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ለድርጅታዊ እንቅስቃሴአቸው የሚረዳ እርዳታ እንዳይደርሣቸው፣ በዚኽ የምርጫ ሂደትም በድርጅቶቹ አባላትና ደጋፊዎች ላይ የሚደርስ መዋከብ፣ ግፍና በደል በውጭው ዓለም እንዳይታወቅ የቻለውን ያኽል ለማፈን በሚደረግ ጥረት የድርጅቶቹ እንቅስቃሴ እስካሁን ከታየውና ከሚታሰበው በላይ ሊታቀብ፣ ሊገታና መውጫ መግቢያ ሊያጣ ይችላል፡፡

5. በአንድ በኩል ጠንካራና ሁነኛ ተፎካካሪ እንዳይኖር የሚቻለውን ሁሉ ሲያደርግ ግን በሌላ በኩል ምርጫውን 'ብቻውን ሮጦ ብቻውን አቸነፈ' እንዳይባልና 'ተቃዋሚው የተሣተፈበት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ' ነው እንዲባል 'ተቃዋሚ' ሆነው የሚሣተፉ ድርጅቶች እንዲኖሩ ተሰልቶ ተቀምጧል ማለትር ይቻላል፡፡ ከነኝህ “ተቃዋሚዎችም” መኻል ዋነኞቹ እነማን እንደሆኑና ምን ያኽል መቀመጫም እንደሚኖራቸው ተተምኖ እንደተቀመጠ መገመት አስቸጋሪ አይደለም፡፡ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው አንድ ምርጫ ነፃና ሃቀኛ መሆኑ የሚታወቀው በምርጫው ቀን በሚታየው ውጤት ሣይሆን በሂደቱና በዝግጅቱ ስለሆነ፣ በአሁኑ ጊዜ ተቃዋሚው ክፍል ያለውን አማራጭ ለሕዝብ አቅርቦ፣ ከሕዝብ ጋር እየተወያየና ሕዝብም አማራጮቹን እንዲመዝን የሚያስችለው ሁኔታ ሊፈጠር ቀርቶ ትንንሽ የአዳራሽ ስብሰባዎች ማድረግ እንኳ እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ ያለበት ሁኔታ ውስጥ ስላለን የቀጣዩ ምርጫ ውጤት ብቻ ሣይሆን ከአሁን ጀምሮ ያለው ሂደትም ከወዲሁ የተወሰነ አድርገን ነው መቁጠር የምንችለው፡፡

6. ልዩና አስገዳጅ ሁኔታ ተከስቶ ምርጫው እስካልተሰረዘ ድረስ እንግዲኽ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በቀጣዩ ምርጫ እንደገና “አቸናፊ” ሆኖ የሚቀርበው ሕወሓት/ኢሕአዴግ ይሆናል፣ ጠቅላይ ሚንስትሩም “የተቀቡት” አቶ መለስ ይሆናሉ፡፡

7. የውጭው ዓለምም ይኽንን “አዲስ ተመራጭ” መንግሥት የመቀበልና አዘቦታዊ ግንኙነቱን መቀጠሉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም ለአዲስ ዙር ሰቆቃና ፍዳውን ለመቁጠር እራሱን “ማዘጋጀት” የሚገደድበት ሁኔታ ይመጣል ማለት ነው፡፡

ጥያቄው ታዲያ ተቃዋሚው ይኽንን ከምናልባታዊነት የጠነከረው ሁኔታ እንዳይደርስ ለማድረግ ሁኔታው አይፈቅድለትም ቢባል እንኳ ሌላ ምን ማድረግ ይችላል፣ ይጠበቅበታልስ? የሚል ይሆናል፡፡

በአዴኀአን እምነት ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለትን በተመለከተ ተቃዋሚው የሚከተሉት ምርጫዎች ይኖሩታል፡፡

አንደኛ፡- በተቃዋሚው ጎራ ያለው ከተጠናወተው የግልና የተናጠል ጉዞ ተላቆና እርስ-በርስ መናቆሩን አቁሞ ምርጫው ዓለም-አቀፍ መሥፈርቶችን ባሟላ መልኩ ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን በአንድ የተግባር አጀንዳ ሥር ተሰባስቦ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ አሁን በአለው የፖለቲካ ድርጅቶች ስብጥርጥሩ የወጣ ሁኔታ ይኽን ማድረግ ቢያንስ ቢያንስ እጅግ አስቸጋሪ እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ባሉ ድርጅቶች መኻል ያለው መቀራረብ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የተራራቀና ቅጥ በሌለው ቅራኔ ውስጥ የተዘፈቀ ነው፡፡ በአገር ውስጥ ባሉ ድርጅቶች መኻል በተወሰነ ደረጃ በተለይ 'በመድረክ' ዙሪያ መሰባሰብ ቢታይም አጠቃላይ ይዞታው የአገሪቱ ሁኔታ በሚጠይቀውና አገዛዙ ላይ ጫና ሊፈጥር ወይም ሕዝብ ሙሉ አመኔታውን ሊሰጠው በሚችልበት ደረጃ ላይ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ለጋራ ትግሉ ሰፋ ያለ አስተዋፆ ማድረግ የሚችሉ አንዳንድ ድርጅቶችም ወደ ጋራው ትግል ሲያተኩሩ አይታይም:: አንዳንዶችም በውስጣቸው በተከሰቱ አሳዛኝ ትርምሶች ምክንያት እንዲዳከሙ እየተደረገ መሆኑ በድርጅቶች መሰባሰብ ላይ አሉታዊ ጫና ማሳደሩ፣ የሕዝባችንን መንፈስ እየጎዳውና ተስፋውን እያመነመነው መሄዱ አልቀረም:: ለተቃዋሚው ክፍል ግን፣ በተለይ በአገር ውስጥ ላለው፣ በሌላ የመታገያ ነጥብ ዙሪያ ለመሰባሰብ ከሚደረግ ጥረት ይበልጥ ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን ሁኔታዎች እንዲሟሉ የጋራ ትግል ለማድረግ በዚኽ አጀንዳ ዙሪያ መሰባሰብ የበለጠ ተፈላጊና ጠቀሜታውም ለሁሉም እንደሚሆን መገመት አያዳግትም:: በውጭው ያለው የተቃዋሚ ክፍልም በዚኽ አጀንዳ ዙሪያ መሰባሰቡና በአገር ውስጥ ካለው ጋር በተቀናበረ መልክ መሥራቱ የተሻለ ውጤት እንደሚኖረው ግልፅ ነው:: ውጤቱ ደግሞ በዚኽ ምርጫ ከሚደረግ ጥረት አኳያ ብቻ የሚታይ ሣይሆን በመኻከላቸው ያለውን የተሸረሸረ ግንኙነት ጠግነው በአገራችን በእርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ አዲስ የሽግግር ሂደት ለመጀመር መልካም መንደርደሪያ ሊሆን ይችላል::

ስለዚኽ ለተቃዋሚው ክፍል ያለው የመጀመሪያ ተግባር ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን በጋራ መንቀሳቀስ ይሆናል:: ምርጫው ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆንም ተቃዋሚው የሚከተሉት እንዲሟሉ በጋራ ሊንቀሳቀስ ይገባዋል::

ሀ- ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ እንዲሆን፣
ለ- የምርጫ ሕጎች ዓለም-አቀፍ የነፃና ርቱዓዊ ምርጫ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ማድረግ፣
ሐ- የፍትኅ ክፍሉ ገለልተኛና ነፃ እንዲሆን፣
መ- መገናኛ-ብዙኃን ከገዥው ፓርቲ መሉና ብቸኛ ቁጥጥር ሥር እንዲወጡና ነፃው ፕረስ ያለ መንግሥት ጣልቃ-ገብነትና ጫና እንዲሠራ ማስቻል፣
ሠ- የፖሊስና ፀጥታ ክፍሉ ከመንግሥት መሉ ቁጥጥር ሥር እንዲወጣ፣
ረ- የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ፣
ሰ - የምርጫውን ሂደትና ክንዋኔ የሚከታተሉ የውጭም ሆነ የውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች እንዲገኙ፣ ወዘተ..

ማንኛውም ምርጫ ነፃና ርቱዓዊ፣ ፍትኃዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆንና ትርጉም ያለው እንዲሆን እነዚኽ ሊተኮርባቸው ከሚገቡ ዓይነታ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ምንም እንኳ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉት ዴሞክራትና አገር-ወዳድ ኃይሎች የአስተሳሰብ፣ የዓላማና የአመለካከት አንድነት ላይ የተመሠረተ አንድነት እንዲኖራቸው፣ ቢያንስ የጋራ መታገያ ጠንካራ የትብብር መድረክ እንዲፈጥሩ ድርጅታችን አጥብቆ የሚያምንበትና ለዚኽም የበኩሉን ያልተቆጠበ ጥረት ለማድረግ ውሳኔው ቢሆንም፤ በአሁኑ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታና ተቃዋሚው ጎራ ያለበት የተሰበጣጠረና የተበተነ አሰላለፍን ስንመለከት ተቃዋሚው ጎራ በተለይ ባለው አጭር ጊዜ ውስጥ አንድ ላይ ሆኖ በቀጣዩ ምርጫ በአንድ ግንባር ሥር ይሰለፋል የሚል ብዥታ አይኖረንም:: ሆኖም ምርጫውን እንደ አንድ አካል ሆኖ ገዥውን ፓርቲ መፈታተንና ለጋራ ውጤት መብቃት አይቻልም ተብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥም ይሁን "የራሱ ጉዳይ አያገባንም" ሊባል፣ ወይም ሁሉም ባሻው መንገድ የየግል መንገዱን ተከትሎ በምርጫው ሂደት በተናጠል መቆምና በግሉ ተወዳድሮ "የሚችለውን ያኽል" የፓርላማ መቀመጫ ለማግኘት መጣር ጠቀሜታው ውሱን፣ ውጤቱም የማያወላዳና ለወደፊት በተቃዋሚው ጎራ የሚኖረው ትሥሥር ላይ የበለጠ መፈራረቅን የሚያስከት፣ ከሁሉም በላይ ግን በአገራችን ዴሞክራሲ መሠረት እንዲይዝ የማይረዳ አካሄድ እንደሆነ ይገነዘቧል::

ምናልባት አንዳንድ ድርጅቶች አሁን ለጊዜው አንዱ ከሌላው የተሻለ አቅም እንዳለው በመገመትና እንቅስቃሴአቸውም በብዙ የአገሪቱ አካባቢዎች የተዳረሰ ወይም በተወሰነ አካባቢም ቢሆን አንፃራዊ ጥንካሬ እንዳላቸው በማሰብ በተናጠል መንቀሳቀሱንና አልፎም

ከአገዛዙ (ከገዥው ፓርቲ) ጋር የተናጠል ድርድር እስከማድረግ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ ያ ሁሉ ግን ዴሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ የሚደረግ ልፋት ስለሆነ የተከፈተው ጽ/ቤት (ቢሮ)ም ሆነ የሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ በአገዛዙ ካድሬዎች አንድ የስልክ ጥሪ ወይም ቀጭን ትዕዛዝ ያለምንም ጥያቄ ወይም ማስጠንቀቂያ ከመቅጽበት ሊዘጋና ቀጥ ሊል ይችላል፡፡ አባላትም እንደተለመደው ሊንገላቱና ታፍሰው ሊታጎሩ ይችላሉ፡፡

ከሕዝብ ጀርባ በድብቅ፣ በተናጠልና በተበተነ መልክ የሚደረግ ድርድርም እንዲሁ እርባና ቢስ ብቻ ሣይሆን በተቃዋሚው ጎራ ባሉ ድርጅቶች መኻል ይበልጥ መፈራቀቅ እንዲኖር የሚያደርግና ጠቀሜታውም ለገዥው ክፍል ብቻ እንደሚሆን ሊታወቅ ይገባል፡፡ በዚኽ መልክ ማንም ተጠቃሚ፣ ማንም የተሻለ ሆኖ ሊገኝና ከሁሉም በላይ ግን ሕዝባችን የሥልጣኑ ባለቤት ሊያደርገው የሚችል ውጤትን አያስገኝም፡፡

ምርጫው ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና ፍትኃዊ እንዲሆን በጋራ መሰለፍና መንቀሳቀስ ግን ትኩረቱ ሂደቱ ላይ ስለሆነና ይኸም በአገራችን ዴሞክራሲ ጥሩ መሠረት ላይ እንዲቆም ስለሚያስችል ጠቀሜታው ለሁሉም - በተናጠል ልሩጥ ብሎ ለሚያስብም ይሁን የጋራ ውጤት ለማስመዝገብ ለተሰባሰቡ ወገኖች እንዲሁም ሰላማዊ ትግል አክትሞለታል ለሚለው ሁሉና አልፎም አሁን በጊዜያዊ ጥቅማ-ጥቅሞችና በግብዝ አመለካከት ምክንያት ተጨፍኖባቸው እንጂ ለራሱ ለገዥው ፓርቲ ጭምር መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

<u>በአሁኑ ጊዜ ተቃዋሚው ክፍል ከገዥው ክፍል ጋር ለማድረግ የሚሞከረው የተናጠል ድርድርም ሆነ በተለይም ደግሞ የድርድሩ ርዕሰ-ጉዳይ "በምርጫው ሥነ-ምግባር" ላይ እንዲሆን መሞከሩ አላስፈላጊ ብቻ ሣይሆን "ጋሪውን ከፈረሱ ያስቀደመ" ከባድ ስህተትና እጅግ አደገኛ አካሄድ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ድርድር ካለ አንደኛ በጋራ እንዲሆን የተቻለው ቢደረግ ቢያንስ ግን ድርድሩ ምርጫው ነፃና ርቱዓዊ ስለሚሆንበት እንጂ ከዚያ ውጭ የሚያልፍ ሊሆን ፈጽሞ አይገባውም፡፡</u>

እንደኛው አገር በዴሞክራሲ እጦትና በአናሳ ቡድኖች ግፈኛ አገዛዝ ትታመስ የነበረችውና ውጥንቅጡ በወጣ ብትብጥ ውስጥ የመዘፈቅ አደጋ ያንዣበበባት ደቡብ አፍሪቃ ዘረኛውንና ኋላ-ቀሩን የአፓርታይድ ሥርዓት አስወግዶ ሁሉን-ጠቀም የሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከተከለው የደቡብ አፍሪቃ መራር ትግል ብዙ መማር ይቻላል፡፡ እንደሚታወቀው ስብጥርጥሩ በወጣ አሰላለፍ ይገኝ የነበረው የደቡብ አፍሪቃ ፀረ-አፓርታይድ ትግል ቅደም-ተከተሉን አንጥሮ በመለየት የትግል ስልቱንና አካሄዱን ማስተካከል ባይችል ኖሮ ደቡብ አፍሪቃ ከዘግናኝ የእርስ-በርስ ትርምስ ተርፋ አሁን ባለችበት የተረጋጋና የአፍሪቃ ኃያል አገር መሆን አትችልም ነበር፡፡ በነጮች የሚመራው ዘረኛው የአፓርታይድ መንግሥት በውጭና በውስጥ የተቀናበረ ግፊት ሥልጣን መጋራት እየተገደደ በነበረበት ሁኔታ የአፍሪቃ ብሔራዊ ኮንግረስና ሌሎች ሃያ ስድስት የሚሆኑ ድርጅቶች ተሰበጣጥረው በነበሩበት ሁኔታ ግንባር ፈጥረውም ይሁን በተናጠል ዘረኛውን መንግሥት ለመጣል ወዲያውኑ ምርጫ ውስጥ ዘው ብለው አልገቡም፡፡ ሁሉም ተቻችለው በእኩልነት የሚሳተፉበትና የሚሠሩበት ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ በአገራቸው ስላልነበር አንድ ላይ መቆም እንደማይችሉ በሚገባ ተረድተውታል፡፡ በዚያ ሁኔታ ደግሞ መሠረታዊ ለውጥ መምጣት እንደማይቻል ተገንዝበዋል፡፡ ስለሆነም በሌላ ሁኔታ ገዥውን የነጮች ዘረኛ ፓርቲ አንድ ላይ ሆነው ለመፎካከር በመሞከርና ዘለቄታዊ ውጤት በማይኖረው ወዲያውኑ ሊገኝ በሚችል ሥልጣን ላይ ከማተኮራቸው ይልቅ የመጀመሪያው እርምጃቸው በቅድሚያ በአገራቸው ላይ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎች እውን እንዲሆኑ ሁሉም በጋራ መቆምና መሥራት እንዳለባቸው ነው ያመኑት፣ የወሰኑትና በጋራ የተንቀሳቀሱት፡፡ ከዚኽ መሠረት ላይ ቆመው ነው ከምርጫ በፊት የነጩን አናሣ ገዥ ቡድን ከላይ ከሀ እስከ ሰ የተጠቀሱት እንዲሟሉ ማድረግና የተደረገው ታሪካዊ ምርጫ የደቡብ አፍሪቃ ሕዝብ ሙሉ ተሣትፎ ማድረግና የሥልጣኑ ብቸኛ ባለቤት እንዲሆንና በአገራቸውም ዴሞክራሲ ጠንካራ መሠረት ላይ እንዲቆም ያስቻሉት፡፡ ያ መሆን በመቻሉም ተጠቃሚ የሆኑት

በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፈው ብቻ ሣይሆን የአፓርታይድ ዘረኛ ሥርዓት አራማጅ የነበረው ገዥ ፓርቲ ጭምር ነው። አቸናፊዎቹ ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች መሆን ቻሉ፣ ዴሞክራሲን ጠንካራ መሠረት ላይ አቆሙ፣ አገራቸውንም ከትርምስ አዳኑ።

በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና ሕዝባችን ከቀጣይ የሰብዓዊ መብት ረገጣና የችግር አዙሪት እንዲላቀቅ ከተፈለገ በተቃዋሚ ክፍል ያለው ወገንም ሆነ ቢቻል ኖሮ ገዥው ፓርቲ ጭምር የትኩረታቸው አቅጣጫ በየበኩላቸው በየጊዜው በሚደረግ ምርጫ ላይም ይሁን ከሱ ከሚገኘው የተናጠል ጊዜያዊ ጥቅም አኳያ ብቻ ሣይሆን መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግና ኅብረተሰባችንን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማሸጋገር ስለሚቻልበት መሆን ይኖርበታል።

በመሆኑም በተለይ በተቃዋሚው ጎራ የቆሙ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ቀጣዩን ምርጫ ማየት የሚኖርባቸው በተናጠል መገኘት ስለሚችል ጊዜያዊ ፖለቲካዊ ጥቅምም ሆነ በገዥው ፓርቲ ላይ ካለን አመለካከት ሣይሆን ሂደቱ ላይ በማተኮር በአገራችን የሰፈነው የአምባ-ገነኖችን አዙሪት ከመስበርና ሕዝባችንን ከቀጣይ ሰቆቃ ከማላቀቅ አኳያ መደረግ ስለሚቻልና መወሰድ ስለሚገባ እርምጃ መሆን ይኖርበታል። ይኸንን ካለማድረግ ጊዜያዊ ተጠቃሚው ገዥው ፓርቲ ሊሆን ቢችልም በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ እንዲኖር በጋራ ባለመታገላችን ተጎጅው ለስቃይ የተዳረገው ሕዝባችን እንደሚሆን ግን ጥርጥር የለውም።

በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ያሉ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን ሁሉ ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን ሁኔታዎች እንዲሟሉ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ቢቻል በአንድ ቅንብር ሥር ቢያንስ በተናበበ መልክ በየአቅጣጫው ሊገፋበት ይችላል፣ ይገባልም።

በአገር ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ሁሉ ገዥው ፓርቲ ጋር የሚያደርጉት ድርድር ምርጫውን ነፃና ርቱዓዊ ስለሚሆንበት የቅድመ-ሁኔታ መብቶች መከበርን በተመለከተ እንዲሆን በማድረግ፣ ከአገር ውጭ የሚገኙት ደግሞ ኅብረተሰቡን በተደራጀ መልክ በማንቀሳቀስ በተለይ እርዳታ ለጋሽ አገሮች ለአገዛዙ የሚሰጡት እርዳታ በቀጥታ ምርጫው ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲሟሉ በተግባር የሚታይ ጭብጥ ውጤት ጋር የተሣሰረ እንዲሆን በማድረግ፣ የውጭ ታዛቢዎች እንዲገቡና ምናልባትም አገዛዙ ይረዱኛል (ቢያንስ አይጋፉኝም) ብሎ የሚያስባቸውን እንዲገቡ የማይከለክላቸው እንደ ካርተር ማዕከል የመሣሰሉት ተቋሞች በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉና የተሟላ መረጃ እንዲይዙ በማድረግ፣ በማሳሰብና በመወትወት፣ አገዛዙ በምርጫው ሂደት የሚያደርገውን ሕገ-ወጥ ተግባር አጉልቶ ለማሳየት በመቻል፣ ወዘተ. መንቀሳቀስ ይቻላል። ይኸ ሁሉ የሚደረገው ግን የምርጫውን ውጤት እንደማይለውጠው እየታወቀ ነው። ለምን ቢሉ መጀመሪያውኑም የዚኸ አካሄድ ዋናው ትኩረቱ ሂደቱ ላይ ስለሆነ የዚኸ እርብርብ ጠቀሜታውም መታየት ያለበት ከዚያና ከዚያ አኳያ መሆን ስለሚኖርበት ነው። ጉዳዩ መመዘን ያለበት አያገባኝም ብሎ በይተዋርነት ከመመልከትም ይሁን ተበታትኖ ከመቅረብ፣ ይኸንን በማድረግ በገዥው ፓርቲ ላይ የሚያደርሰውን ጫና፣ በተቃዋሚው ጎራ ሊፈጥር የሚችለውን የመቀራረብ ሁኔታና በተለይም ከዴሞክራሲያ ሂደት መጠናከር አኳያ ነው።

ሁለተኛ፡- ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለትን በተመለከተ ተቃዋሚው ክፍል ሊከተለው (ሊወስደው) የሚችል ሌላ መንገድ በምርጫው እንደማይሳተፍ ወስኖ ከወዲሁ እራስን ማግለል ካሉት ሁለት ደረጃዎች የመጀመሪያውን ማድረግ ማለት ከሂደቱ ጨዋታ እራሱን ማግለል ይኖርበታል ማለት ነው።

ይኸ በአሁኑ ጊዜ በሁለት ምክንያቶች ውጤት አይኖረውም። የመጀመሪያው እራስን ማግለል (ቦይኮት ማድረግ) ውጤት የሚኖረው የፖለቲካ ድርጅቶቹ አንድ ላይ

*የሚንቀሳቀሱና በአንድ አፍ የሚናገሩ ሲሆን፣ ሁለተኛው ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ትግል በሚደረግበት ሁኔታ ያ እራስን ማግለል ተወዳዳሪውን ብቻ ሣይሆን ዋናውን ባለጉዳይ እራሱን መራጩን ሕዝብ ጭምር በራስ ፈቃድ ከምርጫው የመገለል (የመታቀብ) ውሳኔ ላይ የሚያሳትፍ ሲሆን ነው። አሁን በአገራችን ያለው እውነታ ግን በሁለቱም ረገድ ከዚኽ የተለየ ነው። በተጨማሪም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ለሕዝብና በሕዝብ ምክንያት ሣይሆን በራሣቸው ምክንያት ማንም ምን አለ ምን በዚኽ ምርጫ ለመሣተፍና "ታሪካዊ ሚናቸውን" ለመጫዎች የተዘጋጁ ወዶ-ገብ ድርጅቶች ስለሚኖሩ፣ ገዥው ፓርቲ "በተቃዋሚነት" የሚያሳያቸው (የሚያቀርባቸው) ድርጅቶች እስካሉ ድረስ ደግሞ ከሂደቱ እራስን የማግለሉ ሁኔታ ለዘለቄታው ትግልም እንኳ ባይሆን ምርጫው እንበለ መድብለ-ፓርቲ ውድድር የተደረገ ነው ለሚለው የገዥውን ፀረ-ነፃ ውድድር አቋምና እራቁትነቱን በማጋለጥ ረገድ ለሚደረገው ትግል ጠቀሜታው ደካማ ነው።*

*ሦስተኛ:- የምርጫው ውጤት ከወዲሁ የታወቀና ድርጅቶች መንቀሳቀስ የሚችሉበት ሁኔታም በጣም እየጠበበ እንደሚሄድ ቢታወቅም፣ ከዘለቄታው ትግል አኳያ በሕዝብ መኻል ሆኖ ሕዝባችንን ለማደራጀት እንዲቻል በምርጫው ሂደት ውስጥ እስከሚቻል ተሳታፊ በመሆን በምርጫው ቀን ላለመሳተፍ መወሰን። (ይኽ ምርጫው ሊከናወን አንድ ቀን ሲቀረውም ቢሆን ሊወሰን የሚችል ነው)። ይኽ በቅድሚያ እያንዳንዱ ድርጅት በውስጡና ከተቻለም ተቃዋሚው በጋራ መክሮ ሊወስንበትና አንዱ መወሰደድ የሚችል እርምጃ ነው።*

*አራተኛ:- የምርጫው አቸናፊ፣ "በዋና ተቃዋሚነት" የሚታዩም፣ ሌላውም ሌላውም ውጤት ከወዲሁ አስቀድሞ የተወሰነ እንደሆነ አውቆ በምርጫው ሂደትም በራሱ በምርጫው ክንዋኔም ተሳታፊ መሆን ነው። ከአጠቃላይ ሁኔታው አንፃር ሲታይ ይኽ ውሳኔ (ድርጊት) ገዥው ፓርቲ የሕዝብን ሥልጣን ያለ-አግባብ በጉልበትና በማጭበርበር ቀምቶ ዳግም ቢያንስ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ሕዝባችንን እረግጦ እንዲገዛ ሕጋዊ ሽፋን በመስጠት ተሣታፊ፣ አጋዥና ተባባሪ ሆኖ መገኘት ስለሚሆን አንደኛው አሉታዊ ጎኑ መሆኑ አሌ የማይባል ቢሆንም፣ አንዳንድ ድርጅቶች ያለውን መድረክ ተጠቅመን መቆናጠጥና መድረኩን ሙሉ በሙሉ ለገዥው ፓርቲና ለመሰሎቹ ከመተው ይልቅ ይኽ ምርጫ የሰላማዊ ትግል አካል ስለሆነ ወከባውንና ሌላ ሌላውን ሁሉ ችግር ተቋቁመን የሕዝባችንን ብሶት ለማሰማትና ለዴሞክራሲ ግንባታም መጠነኛ አስተዋፅዖ ማድረግ እንችላለን ብለው የወሰኑ ሊኖሩ ይችላሉ።*

*በእርግጥ የፖለቲካ ድርጅቶች አንድ ላይ ለመንቀሳቀስ ቢወስኑ ቢያንስ ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ላይ የሚኖረው አማራጭ መንገድ የተሻለና ውጤቱም በአጭር ጊዜ በተለይ በውጭና በውስጥ ያለውን ውጥንቅጡ የወጣ የተቃዋሚ ጎራ በማቀራረብና አብሮ እንዲሠራ ዕድል በመስጠት የጋራ ትግሉ እንዲጎለብትና አለፍ ሲልም ለአገራችን የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው አጠያያቂ አይደለም።*

*ከአሁን በፊት በተደጋጋሚ እንዳልነው ሁሉ በሕወሓት/ኢሕአዴግ አካሄድና ይዞታ ሕዝባችንን የሥልጣኑ ባለቤት ለማድረግ የሚያበቃ ነፃና ርቱኣዊ ምርጫ በአሁኑ ጊዜ ይደረጋል ብሎ ማሰብ የማይሆን ነገር ነው። የድርጅቱ የተፈጥሮ ባኅሪም ሆነ የተጓዘባቸው ሂደቶች ይኽን ለማድረግ ቢያንስ ይቸገራል።*

*በዚኽ ረገድ ቀደም ሲል በሰነዳችን ላይ የሚከተለውን ብለን ነበር።*

***"በእኛ እምነት ሁሉም ለውጥ ፈላጊ ኃይል ኢትዮጵያ ነገ የተንኮታኮተች አገር (failed state) ከመሆን ዕጣ ድና፣ አሁን ከምትገኝበት ፈታኝ ሁኔታና አጣብቂኝ ይዞታ ወጥታ ነገ አይደለም የዛሬ ሃያና ሰላሣ ዓመት ምን ዓይነት አገር እንድትሆን እንፈልጋለን? ቁጥራቸው እየጨመረ የሚሄደው ዜጎቻችንስ እየተጣበበ በመጣ ምድር፣ እየከሰመነ በሚሄድ የሕይዎት ማቆያ (መኖሪያ) ምንጭ፣ ተሻሚው እየበዛ በመጣ ጥሬ ሃብት፣ በእውቀትና በሃብት እየተለወጠና***

*እየዳበረ ካለ የዓለም ኅብረተሰብ ጋር በዚህ ዓለም-አቀፋዊ የጥቅምና የግንኙነት መረብ (ግሎባላይዜሽን) አውላላ የፉክክር መድረክ መወዳደር ብቁ እንዲሆኑ የሚያስችል ሁኔታ እየተፈጠረላቸው ነወይ? ዋነኞቹ የሕዝባችን ፍላጎቶችና ጥያቄዎች ምንድን ናቸው? ለሚሉትና ለሌሎችም ተመሳሳይ ክብደት ላላቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች ከስሜታዊነት በራቀና በሰከነ መልክ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።*

*በሕግ ፊት የሁሉም እኩልነት የሚረጋገጥበት ፍትን መኖር፣ የሰብአዊ መብት መከበር፣ መሐይምነትን ማጥፋት፣ ተላላፊ ተውሳኮችን ማስወገድ፣ በቂ ምግብና ንፁህ የመጠጥ ውሃ ማግኘት፣ የትምህርት ዕድል ለሁሉም እንዲኖር ማረጋገጥ፣ የተፈጥሮ ሃብቶቻችንን በአግባቡ መጠበቅና መንከባከብ፣ ፍትኃዊ የኤኮኖሚ ስሪት መዘርጋት፣ ወዘተ... የመሳሰሉ በአገራችን ያሉ ዋና ዋና መሠረታዊና አሳሳቢ የጋራ ችግሮቻችን በአንድ ድርጅት በጎ ፈቃድ ወይም በተወሰኑ ክፍሎች ትግል ብቻ በአስተማማኝ ሁኔታ የሚፈቱና እውን የሚሆኑ አይደሉም።"*

ድርጅታችን ከዚኽ በላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ባገናዘበ መልኩ ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለትን የሚያየው ከአጭር ጊዜ ስልታዊ ጠቀሜታዎችም ይሁን በሌሎች ድርጅቶች አይደገፍም ከሚል የምን-ይሉኝ አጉል ፖለቲካ እራሱን ሳያስጨንቅ ለቆመበት የአገር አንድነትና የሕዝብ ሁለንተናዊ መብቶች መጎናፀፍ ልዕለ-ግብ የሚያደርገውን ትግል ወደ-ፊት ከማራመድና ከማገዝ አኳያ ነው።

ጥያቄው ግን በተለይ ለአዎንታዊ ለውጥ የቆሙ ዴሞክራትና አገር-ወዳድ ኃይሎች ይኽን ኢሕአዴግ ለኢሕአዴግ ያዘጋጀውን ምርጫ እንዴት ያዩታል፣ ምን ማድረግስ ይጠበቅባቸዋል? የሚለው ነው።

"ውጤቱ አስቀድሞ ከወዲሁ በተወሰነ የምርጫ ጨዋታ ውስጥ ምን ማድረግ ይቻላል? የለውጡ ኃይል ምንስ ጉዳዬ ብሎ ጊዜውን ሊያጠፋበት ይገባል?፣ ወዘተ..." ሊባል ይችላል። ጥያቄው በዚኽ መልክ እንዲቀረፅና ሁኔታውን በምርጫው ላይ በተናጠል ለማንጠልጠል ከታሰበ፣ አዎን ልክ ነው የለውጡ ኃይል "ጊዜውን የሚያጠፋበት" ጉዳይ አይሆንም። ጉዳዩ ግን እንዲሁ በቁንፅል ሕወሓት/ኢሕአዴግ እራሱ ለራሱ ባዘጋጀው ምርጫ እሱ እራሱ ይጨነቅበት፣ በዚኽ የምርጫ ግርግር "ጊዜ አናጠፋም"፣ "አይሞቀን፣አይበርደን" ማለት ግን አርቆ ያላየና የዴሞክራሲ ሥርዓት ሂደት መሆኑን የዘነጋ የትግል ትልም (ስትራተጂ) ዝንፈት ይመስለናል።

ቀደም ሲልም እንደጠቃቀስነው ሁሉ አገራችንን ወደከፋ ትርምስ የሚወስዱ ቋፍ ላይ ያሉ ሁኔታዎች በላይዋ ላይ አጥልተው ስለሚገኙ በማንኛውም ጊዜ ይኽ አደጋን ያዘለ ደመና የችግር ዶፉን በሕዝባችን ላይ ከማውረዱ በፊት ቅን-አሳቢና ተቆርቋሪ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያዊ ሁሉ አጥብቆ ሊያስብበት ይገባል። በዚኽ ረገድ በተለይ በፖለቲካው መስክ የተደራጁ ክፍሎች ከፍተኛ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።

ስለሆነም በኛ እምነት ቀጣዩ ምርጫ (ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት) መታየት የሚኖርበት በድርጅቶች በኩል ተራ የሥልጣን ዝውውርን ከማስገኘትም ሆነ በግለሰቦች በኩል ደግሞ በምርጫው ተወዳድሮ በሕዝብ ተወካይ ስም የሥራ ዋስትና ከማስገኘት አንፃር ሣይሆን በቅድሚያ ምርጫውን ተከትሎና ከሱም ተያይዞ በሚከሰቱ ችግሮች ምክንያት አገራችንንና ሕዝባችንን ወደባሰ ቀውስ ውስጥ የሚወስድ ሁኔታን ከማስወገድና ከማርገብ እንዲሁም ጉዳዩ ምርጫው ይዞት ከሚወጣው ውጤት ይበልጥ ጠቃሚውና በጣም ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ነገር ራሱ ሂደቱ ላይ ስለሆነ በአገዛዙ አርቆ-ያላየ ፖሊሲ ድርጊት ምክንያት ፈር የለቀቀውና ቅታው እንዲጠፋ እየተደረገ ያለው የዴሞክራሲ ሂደት መልክ እንዲይዝ፣ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚደረገው ማዝገም ብዙ መንገዳገድን፣ መውደቅ መነሣትን እንዲጠይቅ ተደርጓልና ይኽ ምርጫም ለዚኽ ጉዞ የሚኖረውን አስተዋፅዖ ባስተባቃና ታሳቢ ባደረገ መልኩ መቃኘት ይኖርበታል።

አገዛዙ “ተቃዋሚው የተሣተፈበት ምርጫ ተደረገ” ለማለትና ዴሞክራሲ አለ ለማሰኘት በአብነት የሚጠቀሱና በሽፋንነት የሚያገለግሉት የተወሰኑ ድርጅቶች እስከተሰለፉለት ወይም እስካዘጋጀ ድረስ፣ ዞሮ ዞሮ ጭንቀቱ፤ ስሊቱና ግቡ እንደምንም በሥልጣን ላይ መቆየት ብቻ ስለሆነ፣ ይኸን ምርጫ በአገሪቱ ላይ ያንዣበቡ አደጋዎችን ከማስወገድም ይሁን ዴሞክራሲ በአገራችን ሥር እንዲሰድ ከማሰብ አኳያ የሚጨነቅበት እንዳልሆነ ግልፅ ነው። ይኸም በመሆኑ ነው ለአዎንታዊ ለውጥ የቆሙ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ሁሉ ይኸ የምርጫ ሂደት በአገራችን ያለውን ሁኔታ ለመለወጥ የሚደረገው ትግል ሕዝቡን ማዕከል ላደረገ እንቅስቃሴ የተሻለ ሁኔታን በመፍጠር ሚዛኑ ወደ ተቃዋሚው እንዲያጋድል ከማገዙ አኳያ እንጂ እነሱን ቶሎ ለሥልጣን እንደሚያበቃቸው አድርጎ አቅልሎና አዛብቶ ማየትም ሆነ “የራሱ ጉዳይ” በሚል ኃላፊነት በጎደለው አመለካከት አስፈላጊውን ትኩረት ከመስጠት ወደ-ኋላ ማለትና ችላ ማለት የማይገባቸው።

በአገራችን የነፃና ፍትኃዊ ምርጫ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላት በዚኸ ምርጫ የሚሣተፉትንም ሆነ የማይሣተፉትን ሁሉ እኩል የሚጠቅም እንደሆነ ግልፅ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኀብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) ለአዎንታዊ ለውጥ የቆሙ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ሁሉ ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን በጥሞናና ራቅ-አድርጎ ባዬ መልክና በከፍተኛ የኃላፊነት መንፈስ ማየትና በአፋጣኝ ተመካክረው አንድ የጋራ የተግባር አካል (የነፃና ፍትኃዊ ምርጫ ግብረ-ኃይል) በመሰየም የጋራ እንቅስቃሴ በአስቸኳይ እንዲጀምሩ እነሆ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኀብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን)
መስከረም ፪ ሽህ ፪ ዓ/ም